# የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

## የ2014 በጀት ዓመት የተከለሰ BSC ዕቅድ

ጥቅምት 2014 ዓ.ም

ማ ው ጫ

**ምዕራፍ አንድ ........................................................................................................ 3**

1. ተቋማዊ ዳሰሳ (Organizational Assessment) ..................................................... 3

1.1 የኢ.ብ.ኮ ሀገራዊ ሚና ............................................................................. 3

1.2 የሥልጣንና ተግባር ትንተና (Mandate Analysis) .......................................................... 3

1.3 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች ............................. 4

1.3.1 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ተልዕኮ ...................................................... 4

1.3.2 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ራዕይ ...................................................... 4

1.3.3 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እሴቶች ........................................ 5

1.4 የኢ.ብ.ኮ ጥንካሬ፣ ድክመት መልካም አጋጣሚ እና ስጋት ትንተና (SWOT Analysis) . 6

1.5 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቁልፍ ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎች .......... 8

1.6 ተገልጋዮችና ባለ ድርሻ አካላት ............................................................ 14

**ምዕራፍ ሁለት ................................................................................................... 14**

2. የሪፎርሙ የትኩረት መስኮች እንደ መነሻ ............................................................ 14

**ምዕራፍ ሦስት ....................................................................................................... 19**

ውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ ...................................................................................................19

3.1 አገራዊ ሁኔታ እንደመነሻ ................................................................... 19

3.2. የፕረዚዳንቷ ንግግር እንደመነሻ ............................................................ 21

3.3. በሚዲያ ኢንዱስትሪ የተፈጠረ ውድድር እንደመነሻ .............................................. 22

3.4. የህልውና ዘመቻው እንደ መነሻ ........................................................................ 23

**ምዕራፍ አራት .......................................................................................................... 25**

4.1 የኮርፖሬሽኑ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች..............................................25

4.2. ግቦች፣ ዝርዝር ተግባራት እና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ......................................... 28

**ምዕራፍ አምስት ........................................................................................... 40**

5.1 የድጋፍና ክትትል ስርዓት........................................................................ 40

5.2. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች .......................................... 40

**የኢ.ብ.ኮ ሪፎርሙን ማስፈጸሚያ በጀት ዝርዝር .................................................. 42**

## መግቢያ

በ1923 ዓ.ም በአንድ የሬዲዮ እና በ1957 ዓ.ም በአንድ የቴሌቪዥን ቻናል ሥራ የጀመረው የቀድሞው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የአሁኑ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፎ በአሁኑ ሰዓት ሦስት የቴሌቪዥን፣ ሦስት የሬዲዮ ቻናሎችን እንዲሁም ማህበራዊ ሚዲያን በመጨመር እያስተዳደረ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን የሀገር ግንባታን ለመደገፍ በድምጽና በምስል መረጃ ስርጭት ትውልዱን የመቅረጽና የማነጽ ተልዕኮ ያለው የመንግስትና የህዝብ ተቋም ነው፡፡ ተቋሙ በኢትዮጵያ የበኩር ድምጽ የሆነ እና ረጅም ታሪክ ያለው በመሆኑም በብዙ የድልና የሀሴት እንዲሁም የችግርና የፈተና ወቅቶች ከኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ጋር አብሮ የቆየ ተቋም ነው፡፡ ኢ.ብ.ኮ ጠንካራና ተወዳጅ ተቋም የሆንባቸው ወቅቶች ያሉትን ያክል የተቋሙ አገልግሎት ጥራትና ተወዳዳሪነት ያሽቆለቆለበትም ወቅቶችም ነበሩ፡፡ በአሁኑ ወቅትም ኢ.ብ.ኮ በበርካታና ውስብስብ ችግሮች ውስጥ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ ለአብነት ያክልም ከሰው ኃይል ጋር የተያያዙ የፍልሰት፣ ተነሳሽነት ማጣት፣ የደባል ሱስ ተጠቂነት እና የዋና ተልዕኮና ደጋፊ ሠራተኞች አለመመጣጠን ይታያል፡፡ ከይዘት ጋር በተያያዘ ወቅቱን ጠብቆ ፕሮግራሞችን አለማሻሻል፣ ቻናሎች ተወዳጅና አትራፊ አለመሆን፣ በይዘት ላይ አለማተኮርና የይዘት አለመናበብ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ ጊዜው ያለፈባቸው መሳሪዎች መብዛት፣ አስፈላጊው ቁሳቁስና ቴክኖሎጂ በበቂ ሁኔታ አለመሟላት፣ ምቹ የሥራ አከባቢ አለመኖር፣ የቢሮ መጣበብ፣ በቂ ስቱዲዮ አለመኖርና ያሉትም አለመመቾት ወ.ዘ.ተ… ዋና ዋና ተጠቃሽ ተቋማዊ ፈተናዎች ናቸው፡፡

በመሆኑም በእነዚህ ውስብስብ ችግሮች ምክንያት ኢ.ቢ.ሲ በሀገር ደረጃ ከሚገኙ አዳዲስ ሚዲያዎች አንጻር ሲታይ ተወዳዳሪነቱ ቀንሷል፡፡ መንግስትም በሚዲያው ላይ ያለው እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ መጥቷል፡፡ የተቋሙ ሠራተኞች የሥራ ተነሳሽነት ተዳክሟል፡፡ በዚህም ምክንያት ተቋሙ በመቀጠልና ባለመቀጠል፣ በመበተንና በመጠናከር፣ በመለወጥና በመበስበስ መስቀለኛ መንገድ ላይ ይገኛል፡፡ ከሦስት ዓመት በፊት የተጀመረው ሀገራዊ የለውጥ እርምጃ የፈጠረውን መነቃቃት ተቋሙ እንደ መልካም እድል ተጠቅሞ ዘመኑን የሚዋጅ የሚዲያ ተቋም ለመገንባት እዚህ ግባ የሚባል ሪፎርም አላደረገም፡፡ ኢ.ብ.ኮ ከሌሎች ሚዲያዎች በተሻለ ረጅም ታሪክና ልምድ፣ በርካታ የሰው

ኃይልና የሥራ መሳሪዎች እንዲሁም ቁሳዊ የሆኑና ያልሆኑ ተቋማዊ ሀብቶች ያሉት በመሆኑ ሀብቱን በአግባቡ ተጠቅሞ ወደ ተሻለ ምዕራፍ እንዲስፈነጠር የሚያደርግ የአመራር ቅኝትና የሠራተኞች ቁርጠኝነት ያስፈልገዋል፡፡

እነዚህ በርካታ እና ውስብስብ ችግሮችን በዘላቂነት በመፍታት ተቋሙን ከመስቀለኛ መንገድ መንጥቆ በማውጣት ወደ ለውጥ ጎዳና በማሸጋገር ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና ተወዳዳሪ የሚዲያ ተቋም መገንባት የሚያስችል ስትራቴጅ፣ ስልትና የማስፈጸሚያ አቅጣጫዎችን ነድፎ ወደ ውጤት መቀየር የአመራሩ ዋነኛ የቤት ሥራ በመሆኑ ሪፎርም ማድረግ የግድ ሆኗል፡፡ የሪፎርሙ ዓላማም የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የአድማጭ ተመልካቹን ፍላጎት ለማርካት፣ ከሌሎች አቻ የሚዲያ ተቋማት ጋር ተፎካካሪ ሆኖ ለመገኘት፣ በመንግሥትና በህዝብ መካከል ከመቼውም ጊዜ በላይ ድልድይ ሆኖ ለማገልገል እና በአጠቃላይ ቀዳሚ፣ ተመራጭ፣ ተአማኒና ተፅዕኖ ፈጣሪ እንዲሆን በማስቻል ለሀገር ግንባታ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ማድረግ ነው፡፡ አጠቃላይ የሪፎርሙ አላማ የተቋማዊ ባህል ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ይህም ሲባል ከልግመኝነት ወደ ታታሪነት፣ ከምን አገባኝ ወደ ባለቤትነት ስሜት፣ በውጤት መለካት፣ ምቹና ዘመናዊ የሥራ አካባቢ፣ ቀልጣፋና ወረቀት አልባ አሠራር፣ ከቡድንተኝነት ወደ ሀገራዊ ስሜት፣ ፈጠራ የታከለበት የሚዲያ አቀራርብ እንደ ልማድ (continuous innovation) መውሰድን ያካትታል፡፡ በመሆኑም የኢ.ብ.ኮ የ2014ዓ.ም BSC እቅድ የሪፎርሙን ፎኖተ ካርታ ሰነድ መነሻ በማድረግ በቀጣይ ለመድረስ ከታሰበባቸው ግቦች አኳያ ቅኝት በማድረግ እቅዱን መከለስ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. ተቋማዊ ዳሰሳ (Organizational Assessment)

### 1.1 የኢ.ብ.ኮ ሀገራዊ ሚና

የኢ.ብ.ኮ ዋነኛ ሀገራዊ ሚና ለተረጋጋና ለበለጸገ ሀገር ግንባታ ቁልፍ አስተዋጾ ማበርከት ነው፡፡ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገር ግንባታ ላይ የሚሰሩ ተቋማት እንዲጠናከሩ ኢ.ብ.ኮ የበኩሉን ሰፊ ድርሻ መወጣት እንደሚኖርበት በመታመኑ የሪፎርም ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት ወደ ለውጥ ውስጥ ገብቷል፡፡

ሚዲያ ነጻ፣ ገለልተኛና ብቃት ያላቸው ተቋማት እንዲፈጠሩ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት፣ መልካም ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ በማሳወቅ፣ ሙስናና ሌብነትን በማጋለጥ ወ.ዘ.ተ... ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ሚዲያ በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ብሄራዊ መግባባት እንዲፈጠር፣ ብዝሃነትን የሚያከብርና በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ትውልድ እንዲፈጠር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ሚዲያ ለዲሞክራሲ ባህል መዳበር፣ የመነጋገር፣ የመከራከር፣ የመወያየት ልማድ እንዲዳብር የብዝሃ ሃሳብ መንሸራሸሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በጥቅሉ ሚዲያ በተለይም እንደ ኢ.ብ.ኮ ያለ ሀገራዊ ሚዲያ በህዝብና መንግስት መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ በማገልገል የተረጋጋና የበለጸገ ሀገር ለመገንባት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

### 1.2 የሥልጣንና ተግባር ትንተና (Mandate Analysis)

የኢትዮጵያ ሬዲዮ እና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅቶች በየራሳቸው ስያሜ ራሳቸውን ችለው ለረጅም ጊዜ ሲተዳደሩ ከቆዩ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 114/87 አንድ ድርጅት ሆነው እንዲደራጁ ተደርገው ነበር፡፡ የኢዲቶሪያል ነጻነታቸውን ይበልጥ ለመጠበቅና አገልግሎታቸውን በጥራት ለመስጠት እንዲችሉ ታስቦ በአዋጅ ቁጥር 858/2006 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በሚል በአዲስ ተደራጁ፡፡ ይሁን እንጅ ኢ.ብ.ኮ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር አኳያ የሚጠበቅበትን ያህል እየሠራ አልነበረም፡፡ ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋናነትም፣ አዋጁ ሲወጣ ያላካተታቸው ጉዳዮችና ያልመለሳቸው ጥያቄዎች በመኖራቸው፣ አሁን ካለው ሀገራዊና አለማቀፋዊ እንዲሁም የሚዲያ ኢንዱስትሪው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በተልዕኮ እና ዓለማ እንዲሁም በፋይናንስ እና ገቢ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ተመርኩዞ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡በመሆኑም

በመልሶ ማቋቋሚያ አዋጁ ከኮርፖሬሽኑ ዓላማ አንፃር ስንመለከት ካለፈው አዋጅ አላማዎች በተጨማሪ በሀገር ግንባታና በብሔራዊ መግባባት፣ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እውን እንዲሆን ለማስቻል የሚደረገውን ጥረት ማገዝን ጨምሮ ያካተተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተቋሙ ለቀጠናዊ ትስስር የሚኖረውን ሚና ጭምር ታሳቢ ያደረገ ነው፡ ፡ በአጠቃላይ የሪፎርም ማሻሻያዎቹ ኢ.ብ.ኮ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በአግባቡ ለመወጣት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡

## 1.3 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች

### 1.3.1. ተልዕኮ

የድምጽ እና ተንቀሳቃሽ ምስልን በመጠቀም መረጃዎችን አዝናኝና አስተማሪ በሆነ መንገድ በማሰራጨት ሀገራዊ መግባባት የተፈጠረባት፣ ዘላቂ ሰላም የሰፈነባት፣ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ፈርጀ ብዙ ጥረት ውስጥ ቁልፍ ሚና ከመጫወት በተጨማሪም የኢ.ብ.ኮ ተልዕኮ የግል ሚዲያ ሊሸፍናቸው የማይችሉ ጉዳዮችን መሸፈን መሆን ይኖርበታል፡፡ እነዚህም የሀገር ግንባታን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮችን ማለትም ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር፣ ተቋማት እንዲጠናከሩ፣ ዲሞክራሲ እንዲተከልና እንዲጸና በጥቅሉ ብልጽግና እንዲረጋገጥ፣ በማዝናናት፣ ማሳወቅና ማስተማር ተልዕኮው ይሆናል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መጭው ትውልድ ላይ መሥራት፣ ብዝሃነትን ማስተናገድ እና የውጭ ግንኙነት በግል ሚዲያዎች ሊሸፈኑ የማይችሉ ነገር ግን ከሀገራዊ ሚዲያ መንግስት የሚጠብቃቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም፡-

- የመንግስት አቋምንና ፖለቲካዊ እርምጃዎችን ተዓማኒ በሆነ መንገድ ለሕዝብ ማሳወቅ፤
- የሕዝብን ፍላጎት፣ ቅሬታና በደል ለመንግስት ማስረዳት፤
- በሕዝቦች መካከል መቀራረብንና መግባባትን መፍጠር፤
- መጭውን ትውልድ መቅረጽና ማነጽ፤
- በውጭው ዓለም የኢትዮጵያንና የአፍሪካን ድምጽ የሚያስተጋባና የምዕራብ ሚዲያዎች አማራጭ የሚሆን ማድረግ፤
- ንግድ፣ ቱሪዝም እና ኢንቨስትመንትን ማሳለጥ የተቋሙ ዋነኛ ግቦች ይሆናሉ፡

### 1.3.2. ራዕይ

በአፍሪካ ቀንድ ተመራጭ፣ ተወዳጅ፣ ተዓማኒ እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሚዲያ መሆን

### 1.3.3. እሴቶች

- የባለቤትነት ስሜት
- ፈጠራ
- ሙያዊ ነጻነትን በሃላፊነት
- ለኢትዮጵያ

#### 1.3.2.1. የእሴት መገለጫዎች

**የባለቤትነት ስሜት፡-** ሠራተኛው ተቋሙ የኔ ነው የሚል የባለቤትነት መንፈስ ተላብሶ በሚያከናውናቸው ሥራዎች ሁሉ የላቀ አፈጻጸም እንዲኖረው የሚያስችል አሰራሮች ይተገበራሉ፡፡

**ፈጠራ፡-** ሚዲያ ፈጣን በሆነው ተለዋዋጭ የዲጂታል ዓለም ውስጥ ያለ ዘርፍ ነው፡፡ ኢ.ብ.ኮ

ተከታታይነት ያለው በፈጠራ ሥራዎች የታጀበ የአድማጭ ተመልካቹን ቀልብ የሚገዛ ሚዲያ እንዲሆን አልሞና አቅዶ ይሰራል፡፡

**ሙያዊ ነጻነትን በሃላፊነት፡-** ኢ.ብ.ኮ ለባለሙያዎች ያልተገደበ ሙያዊ ነጻነትን ከነተጠያቂነቱ ይሰጣል፡፡

**ለኢትዮጵያ፡-** ባለሙያው የሚሰራው በግልም ሆነ እንደ ተቋም ሀገራዊ ፋይዳ ላይ አስተዋጽኦ እንዳለው ተገንዝቦ ከወገንተኝነት በጸዳ መልኩ በሀገር ማገልገል ስሜት እንዲሰራ ማስቻል፡፡

## 1.4 የኢ.ብ.ኮ ጥንካሬ፣ ድክመት መልካም አጋጣሚ እና ስጋት ትንተና (SWOT Analysis)

ሠንጠረዥ 1:- የኢ.ብ.ኮ ጥንካሬ፣ ድክመት መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች ትንተና (SWOT Analysis)

| የእይታ መስኮች | ጥንካሬ | ድክመት | መልካም አጋጣሚ | ስጋት |
|---|---|---|---|---|
| ተገልጋይ/ ህዝብ | • አዳዲስ የዜና እና ፕሮግራሞች ፎርማት መጀመሩ፣<br>• ኢ.ብ.ኮ ዜና ሰባሪ እየሆነ መምጣቱ፣<br>• በየክልል ከተሞች ዜያዊ ስቱዲዮ ማስፋፋት መጀመሩ፣<br>• የህዝብ ቅሬታዎች ሽፋን እያገኙ መምጣት፣ | • የደንበኞች እርካታ አሁንም የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱ፣<br>• የስርጭት ሽፋንና ጥራት መጓደል መኖሩ፣<br>• በሚዲያው ዘርፍ ያለውን ውድድር በአሸናፊነት ለመወጣት በቴክኖሎጂ ግብአትና ባለሙያው ላይ ብዙ ሥራ መስራት የሚጠበቅ መሆኑ፣ | • በድል ዜናዎች ዘገባ ኢ.ብ.ኮ ቀዳሚ መሆኑ፣<br>• በሀገር ጉዳይ አዳዲስና ሳቢ የሆኑ አቀራረቦች መጀመራቸው፣ | • የግልና የክክል ሚዲያዎች ጠንካራ ተወዳዳሪ ሆነው መቀጠላቸው፣<br>• የባለሙያዎች ፍልሰት መኖሩ እና በቀጣይም አይቀሬ መሆኑ፣ |
| ፋይናንስ | • የውስጥ ገቢ እያደገ መምጣቱ፣<br>• የመንግስት በጀት ድጋፍ እየተሸሻለ መምጣቱ፣<br>• አዳዲስ የገቢ ማስገኛ (ዲጂታል ሚዲያዎች በስፋት ወደ ሥራ መግባታቸው) | • ሁሉም ሚደየሞች የሚጠበቅባቸውን ያህል ገቢ አለማመንጨት፣<br>• የኢ.ብ.ኮ ገቢ በአዲስ አበባ ብቻ የታጠረ መሆኑ<br>• ረጅም ጊዜ የተተራቀመ የዱቤሰነዶች መኖር፣<br>• ከቴሌቪዥን ባለቤትነት ክፍያ የሚገኝ ገቢን አሟጦ አለመሰብሰብ<br>• ውጤታማ ያልሆነየንብረት አያያዝ | • ኢ.ብ.ኮ አዳዲስ አቀራረቦች በመጀመሩ የስፖንሰሮችን ቀልብ መሳባቸው፣<br>• ኢ.ብ.ኮ ሁለንተናዊ ሪፎርም እያካሄደ መሆኑ ተወዳዳሪነቱን ይጨምርለታል፣ | • የመንግስት የበጀት ድጋፍ በህግ ማዕቀፍ አለመደገፉ፣<br>• በወቅታዊ ፕሮግራሞች መጣበብ ምክንያት ማስታወቂያዎች የሚፈለገውን ያህል አለመሄዳቸው፣<br>• የውጭ ምንዛሪ |

| የእይታ መስኮች | ጥንካሬ | ድክመት | መልካም አጋጣሚ | ስጋት |
|---|---|---|---|---|
| | | መኖር፣ | | አቅርቦት ከፍተኛ ችግር መሆኑ፣ |
| የውስጥ አሰራር | • የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች እተሸሻሉ መሆኑ፣ኢ.ብ.ኮ የሪፎርም ትግበራ መጀመሩ፣<br>• የኢ.ብ.ኮ የሪፎርም እቅድ ታቅዶ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ውይይት መደረጉ፣እና በቦርድ መጽደቁ<br>• የማቋቋሚያ አዋጅ መውጣቱ፣ | • ጠንካራ የስራ ባህልና ተጠያቂነት ሥርዓት አለመዳበር፣<br>• ዘርፉ የሚጠይቀው ልምድ ያለው ባለሙያ በበቂ አለመገኘቱ፣<br>• ተከታታይ የሆነ ፈጠራ (ContinuesInnovation) አለመዳበር፣ | • ሊያሰሩ የሚችሉ ሀገራዊ ሪፎርሞች፣ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች መኖራቸው፣ | • የለውጥ ተግዳሮቶች በተቋሙ ሊኖሩ መቻላቸው |
| መማማርና እድገት | • ለኃላፊዎች/ሠራተኞች የሀገርውስጥና የውጭ ትም/ት እድል መመቻቸቱ፣<br>• ለኃላፊዎችና ሠራተኞች የማነቃቂያ ሥልጠና መሰጠቱ እና የኢ.ብ.ኮ የስልጠና ማዕከል በአዲስ እያደራጀ መሆኑ፣ | • የእውቀት ሽግግር ስርዓት ባህል በተቋሙ አለመዳበር፣<br>• በቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ያደረጉ አጫጭር የተግባር ስልጠናዎች አለመጠናከራቸው፣ | • መንግስት ለሰው ኃይል ልማቱ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ፣ | • ባለሙያው በተሰማራበት እየዳበረ የሚሄድ የሥራ ላይ ፈጠራ ተነሳሽነት አናሳ መሆን |

## 1.5 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቁልፍ ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎች

ሠንጠረዥ 2:- የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቁልፍ ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎች

| ተ.ቁ | ቁልፍ ችግሮች | የመፍትሄ እርምጃዎች |
| --- | --- | --- |
| 1 | የህግ ማዕቀፎች እና የአሰራር መመሪያዎች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ማነቆ መሆናቸው፣ | የአዋጅና ደንብ ማሻሻያ ማድረግ፣መመሪያዎችንና አሰራሮችን ከተቋሙ ሪፎርም አንጻር ማሻሻል፣ የመዋቅር ማሻሻያ መስራት፣ |
| 2 | የይዘት ችግሮች(በሕዝብ ዘንድ በቂ ተመልካች የሌላቸውና በይዘት ጥራታቸውና ተዓማኒነታቸው ዝቅተኛ የሆኑ መሆናቸው) | ጣቢያዎቹን በቅደም ተከተል ሪፎርም ማድረግ |
| 3 | የዲጂታል ሚዲያ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች | የዲጂታል ሚድያ ይዘትን ማሻሻል፤ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ላይቭ ስትሪም አዳዲስ ፎርማት ማዘጋጀት፤ የዩቱብ ቻናሉ በስታንዳርድ እንዲመራ ማድረግ፣ብቁ የሰው ሓይል ማሟላት |
| 4 | በሚዲያ ቴክኖሎጂ የሚገጥሙ የቴክኖሎጂ ግብኣት ችግሮችና በአግባቡ ኦፐሬት የሚደርግ የሰለጠነ ባለሙያ ችግር | የቴክኖሎጂ ግብአት ማሟለት፣ ለባለሙያዎች በሀገር ውስጥና በውጭ የሥራ ላይ ስልጠና ማመቻቸት |
| 5 | ከገበያና ብራንዲንግ ጋር የተያያዙ ችግሮች | ኢ.ብ.ኮን በደንብ ማስተዋወቅ፣ደረጃውን የጠበቀ የታዳሚያን ዓይነትና ፍላጎት ጥናት ማካሄድ፣ የተፎካካሪዎችን ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን ማጥናት፣የብራንድ አስተዳደርን ማሻሻልና ማጠናከር፣የገበያ ልማት አስተዳደር የሚያተጉ ዕቅዶችን ማስቀመጥ፣ |
| 6 | የንብረት አጠቃቀምና አስተዳደር ችግር፣የውል አያያዝ ችግር፣ሁሉም ቻናሎች በሚፈለገው ደረጃ ገንዘብ ያለ ማመንጨት ችግር፣ | የላይሰንስ ክፍያ አሰባሰብን ማሻሻል፣ የውል አያያዝን በቴክኖሎጂ መደገፍ፣ የሀብት ብክነትን መከላከል |
| 7 | የአገልግሎትና ሀብት አስተዳደር ችግሮች | በቴክኖሎጂ የታገዘ የንብረት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፣የተቋሙን ሀብቶች መለየትና ጥቅም ላይ ማዋል፣ |
| 8 | አሁን ያለው ኢ.ብ.ኮ ህንጻ ለሥራ አመቺ አለመሆኑ | |

| ተ.ቁ | ቁልፍ ችግሮች | የመፍትሄ እርምጃዎች |
| --- | --- | --- |
| | | ነባሩን ቢሮ በመልቀቅ ሽጎሌ በሚገኘው የሜቴክ ህንጻ ማዘዋር፣ኢንተሪየር ዲዛይን ማሰራት፣ ዘመናዊ ስቱዲዮች ማስገንባት፣ |

### 1.6 ተገልጋዮችና ባለ ድርሻ አካላት

ሠንጠረዥ 3:- ተገልጋዮች

| ተ.ቁ | ተገልጋዮች (customer) | መስፈርቶች | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በገቢ ላይ ያላቸው ተጽዕኖ(revenue impact) | በአገልግሎት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ (influence) | በሚያገኙት አገልግሎት ብዛት (service offered) | የተገልጋዮች/ባለ ድርሻ አካላትመጠን (size) | ለተልዕኮ መሳካት ያላቸው ወሳኝ ሚና (critical role conceninig your mission) | የተገል.ጋይ/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት አንጻራዊ ጠቀሜታ(relative importance of their needs) | ደርጃ(degree of importance) ከ 30 |
| 1 | አድማጭ/ተመልካቾች | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 30 (1ኛ) |
| 2 | የፖለቲካ ፓርቲዎች | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 28 (2ኛ) |
| 3 | የክልልና የፌድራል መንግስታት | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 27 (3ኛ) |
| 4 | በውጭ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች | 5 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 21 (5ኛ) |
| 5 | ህዝባዊ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 3 | 24(4ኛ) |

| ተ.ቁ | ተገልጋዮች (customer) | መስፈርቶች | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በገቢ ላይ ያላቸው ተጽዕኖ(revenue impact) | በአገልግሎት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ (influence) | በሚያገኙት አገልግሎት ብዛት (service offered) | የተገልጋዮች/ባለ ድርሻ አካላትመጠን (size) | ለተልዕኮ መሳካት ያላቸው ወሳኝ ሚና (critical role conceninig your mission) | የተገልጋይ/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት አንጻራዊ ጠቀሜታ(relative importance of their needs) | ደርጃ(degree of importance) ከ 30 |
| 6 | የሀይማኖት ተቋማት | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 17 (7ኛ) |
| 7 | ባንኮችና የግል የንግድ ድርጅቶች | 5 | 4 | 4 | 2 | 2 | 2 | 19 (6ኛ) |
| 8 | ኢምባሲዎችና ቆንስላዎች | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 15(8ኛ) |
| 9 | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች( ሀገር በቀልና አለም አቀፍ ድርጅቶች) | 4 | 3 | 1 | 1 | 1 | 4 | 14 (9ኛ) |

ሠንጠረዥ 4:- ባለድርሻ አካላት

| ተ.ቁ | በላድርሻ አካላት (Stakeholders) | መስፈርቶች | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በገቢ ላይ ያላቸው ተጽዕኖ (revenue impact) | በአገልግሎት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ (influence) | በሚያገኙት አገልግሎት ብዛት (service offered) | የተገልጋዮች / ባለድርሻ አካላትመጠን (size) | ለተልዕኮ መሳካት ያላቸው ወሳኝ ሚና (critical role conceninig your mission) | የተገልጋይ/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት አንጻራዊ ጠቀሜታ (relative importance of their needs) | ደርጃ (degree of importance) ከ 30 |
| 1 | የገንዘብ ሚኒስቴር | 5 | 5 | 3 | 5 | 5 | 4 | 27 (2ኛ) |
| 2 | የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 30 (1ኛ) |
| 3 | የክልሎች መገናኛ ብዙሃን | 3 | 4 | 2 | 3 | 5 | 2 | 19(9ኛ) |
| 4 | የመንግስት ኮሚኬሽን አገልግሎት | 5 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 25 (4ኛ) |
| 5 | ብሔራዊ ባንክ | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 2 | 24 (5ኛ) |
| 6 | የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ | 4 | 5 | 3 | 2 | 5 | 3 | 22 (6ኛ) |
| 7 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ኤጀንሲ | 4 | 5 | 5 | 2 | 3 | 2 | 21 (7ኛ) |
| 8 | ኢ.ዜ.አ | 5 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 20 (8ኛ) |
| 9 | ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 3 | 26(3ኛ) |

| ተ.ቁ | በላድርሻ አካላት (Stakeholders) | መስፈርቶች | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በገቢ ላይ ያላቸው ተጽዕኖ (revenue impact) | በአገልግሎት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ (influence) | በሚያገኙት አገልግሎት ብዛት (service offered) | የተገልጋዮች / ባለድርሻ አካላትመጠን (size) | ለተልዕኮ መሳካት ያላቸው ወሳኝ ሚና (critical role conceninig your mission) | የተገልጋይ/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት አንጻራዊ ጠቀሜታ (relative importance of their needs) | ደርጃ (degree of importance) ከ 30 |
| 10 | የተባባሪ አዘጋጆችና ማስታወቂያ ኤጄንቶች | 5 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 18 (10ኛ) |

# ምዕራፍ ሁለት

## ውስጣዊ ሁኔታ ዳሰሳ

### 2. የሪፎርሙ የትኩረት መስኮች እንደ መነሻ

ሪፎርሙ በዋናናት ኢ.ብ.ኮ ያሉበትን ችግሮች በማላቀቅ ተቋሙ ጠንካራ ተልዕኮ የማስፈጸም አቅም ያለው እና ተወዳደሪ ሚድያ ማድረግን የሚተልም ነው፡፡ ስለዚህም ሪፎርሙ ዋነኛ ችግር ያለበት እና የተወዳዳሪነት አቅም የሚሰጡ ዘርፎች እና ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህም ዋና ዋና ክፍፍቶችን በመለየት የሪፎርም ሀሳቦችን እና ትግበራ ሂደቶችን ያቀርባል፡፡ ዋና ዋና የትኩረት መስኮቹም፡-

#### 2.1 የአሠራር ስርዓትና የሕግ ማሻሻያ

አንድ ተቋም ለመለወጥ የአሠራር ስርዓቱን እንዲሁም የሚመራበትን ሕግና ደንብ ማሻሻል መቻል አለበት፡፡ ኢ.ቢ.ሲ የአሠራር ስርዓትና የሕግ ክፍፍተት እንዳለበት ተቋም ኢ.ቢ.ሲን ለመለወጥ የሚደረገው ሪፎርም ይህን ታሳቢ ማድረግ ያለበት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየዘርፉ ታሳቢ የተደረጉት ሪፎርሞችም በሙሉ ለውጥ እንዲያመጡ መሰረት እንዲይዙ የአሠራር ስርዓትን እና የሕግ ማሻሻያን የሚጠይቁ በመሆናቸው ይህን ተፈጻሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም የተለያዩ ንዑስ የትኩረት መስኮች ያሉ ሲሆን፡- መልሶ ማቋቋሚያ እና ውስጥ አሠራር ደንብ፣መዋቅራዊ ማሻሻያ እና መልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ትኩረት ተደርጎባቸው የሚከናወኑ የሪፎርሙ አካል ናቸው፡፡

#### 2.2 የይዘት ማሻሻያ እንደ መነሻ

ነባሮቹ ጣቢያዎች በሕዝብ ዘንድ በቂ ተመልካች የሌላቸውና በይዘት ጥራታቸውና ተዓማኒነታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ናቸው፡፡ እነዚህን ጣቢያዎች ሪፎርም ለማድረግ በመጀመሪያ ከሀገር ግንባታ አንጻር ቅድሚያ ልንሠጣቸው ከሚገቡ ጣቢያዎች ጀምረን በቀጣይ ደረጃ በደረጃ ሌሎችን ጣቢያዎች ሪፎርም በማድረግ ኢ.ብ.ኮ የሚያስተላልፋቸው የሚዲያ ስርጭቶች በሙሉ ተመራጭ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

### 2.3 የዲጂታል ሚድያ ሪፎርም እንደመነሻ

ዲጂታል ሚዲያ የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን በመጠቀም በድረ-ገጽ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በሞባይል መተግበሪያ አማካኝነት በፅሑፍ፣ በምስልና በፎቶ ያለግዜና ቦታ ገደብ ከየትኛውም አካባቢ መረጃ የሚተላለፍበት ስርዓት ነው፡፡ ይህ የሚዲያ ዘርፍ በተለይም የማህበራዊ ትስስር ገጾች አሁን ላይ ተመራጭ የሚዲያ አመራጭ ዘርፍ ከመሆን አልፎ በሰው ልጆች ሁለንተናዊ ተግባራት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ ኢ.ብ.ኮም የዲጂታል ሚዲያውን ተቀላቅሎ በፌስቡክ 2.5 ሚሊዮን፣ በዩቱብ ከ856 ሺ በላይ ሰብስክራይበር፣ በቴሌግራም 88 ሺ፣ በኢንስታግራም ከ64 ሺ፣ ቲውተር ከ215 ሺ በላይ ተከታይ በማፍራት እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ነገር ግን በዘርፉ ሊፈጠር ከሚችለው አቅምና ዘመኑ ከደረሰበት የሚድያ ኢንዱስትሪ ደረጃና ፍላጎት አንጻር ከፍተት የሚታይበት ነው፡፡ ስለዚህም ኢቢስን ለመለወጥ በሚሠራው ሥራ የዲጂታል ሚድያው ክፍተቶቹን በመለየት መፍትሄዎችን ማምጣት ያስፈልጋል፡፡

### 2.4 የሚድያ ቴክኖሎጂ ማሻሻያ እንደመነሻ

ሚድያ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት እንዲሁም ባለው የቢዝነስ ምህዳር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ሚድያ ቴክኖሎጂ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል፡፡ ሚድያ ቴክኖሎጂ ስንል በአንድ ሚድያ ውስጥ ለማዘጋጀት፣ ለማሰራጨትና ሚድያን ለማስተዳደር የሚያስፈልጉ ሀርድ ዌር፣ ሶፍት ዌር እና የተለያዩ መሳሪያዎችን እንዲሁም መሳሪያዎቹን በአግባቡ መጠቀም የሚችል የሰው ኃይልን የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢ.ብ.ኮ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች እና ብቁ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም የሰው ኃይል ክፍተት የሚታይበት ነው፡፡ በመሆኑም ኢ.ብ.ኮ ለውጥን እንዲያመጣ ከተፈለገ እና ተልዕኮውን በብቃት እንዲወጣ የሚድያ ቴክኖሎጂ ላይ ያለበትን ክፍተት ለመድፈን መሥራት አለበት፡፡

### 2.5 የገበያ ልማት እና ብራንዲንግ ማሻሻያ እንደመነሻ

ኢ.ብ.ኮ በመንግስት በሚሰጠው ተልዕኮ ብቻ ሳይሆን በገበያ የሚመራ የትርፍ ኮርፖሬሽን ተደርጎ የተቋቋመ ቢሆንም የአሠራር ስርዓቶቹና አስተሳሰቡ ከመደበኛ የመንግስት መስሪያ ቤት ያልተላቀቀ ነው። ማንኛውም በገበያ ሕግጋት ተፎካክሮ ለትርፍ የሚሠራ የንግድ ድርጅት ደንበኞቹን መሳብና ማቆየት ተቀዳሚ ተግባሩ ነው። ተፎካካሪ በሚበዛበት

የቢዝነሱ ዓለም ትርፋማ ሆኖ መዝለቅ የሚቻለው ደንበኛን ማርካት ብቻ ሳይሆን ከተፎካካሪ አስበልጦ በማርካት ጭምር መሆኑ ይታወቃል። ይህ ደግሞ በገበያው ላይ የሚገኘውን ደንበኛ ዓይነትና ፍላጎቶቹን በየግዜው በጥናት መለየትና መማወቅ ይጠይቃል።

የሚድያው ፕሮግራሞች ታዳሚያ ናቸው። ሚድያ የሚያመርተው ይዘት ሰፊ ታዳሚአግኝቶ ትርፋማ እንዲሆን ከተፈለገ የሚድያውን ስርጭት የሚከታተለው ታዳሚ ዓይነትና ፍላጎት ጥናት ወሳኝ ነው።

ከገበያ ልማት አንጻር ስንመለከተው በኢ.ብ.ኮ ያለውን ችግር ስንመለከት ችግሩ ገበያ ልማት (marketing) በተሳሳተ ከመረዳት ይጀምራል። ኢ.ብ.ኮ የገበያ ልማት አድርጎ የሚወስደው የስፖንሰርሺፕና የአየር ግዜ ኪራይን ነው። ሽያጭ በባህሪው የሻጭን ፍላጎት የሚያስቀድም ተግባር በመሆኑ ደንበኛ የጉዳዩ ማዕከል አይሆንም። በዚህም ነው የኢ.ብ.ኮ የገበያ ልማት ትኩረት ታዳሚዎቹን የሚያበዛና የሚይዝ ፕሮግራም ከማዘጋጀት ይልቅ ገቢ መሰብሰብ ላይ ያተኮረ የአየር ግዜ ሽያጭን ያስቀደመው። የሚድያ ምህዳሩ ሰፍቶ ፉክክሩ በበረታበት በዚህ ግዜ ታዳሚ የሚፈልጋቸውን ጥራት ያላቸው ይዘቶች በመተው፣ በኢ.ቢ.ሲ ሞኖፖሊ ዘመን በነበረው አስተሳሰብ የኢ.ቢ.ሲ ታዳሚዎችን ፍላጎት ሳያስተናግዱ፣ ገቢን ማሳደግ አይቻልም። የአድማጭ/ተመልካችን ፍላጎት በማርካት የሚድያ ታዳሚን በማብዛት፣ ከዚያ ገቢን ማሳደግ ይቻላል፡፡

### 2.6 የፋይናንስ ማሻሻያ እንደመነሻ

ሚድያ በአንድ በኩል ለአስተዳደራዊ እና ለሚድያ ቴክኖሎጂዎች ወጪ ብዙ ገንዘብ የሚያስፈልገው ከመሆኑ፤ በሌላ በኩል ገቢ የሚያመነጭ ተቋም እንደመሆኑ ፋይናንስና ፋይናንስ አስተዳደሩ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ፋይናንስ የሚድያ ይዘት፣ የቴክኖሎጂ፣ የጥናት እና ሌሎች ጉዳዮች የጀርባ አጥንት በመሆን በጥራት፣ በተደራሽነት እና ተልዕኮን በመወጣት ላይ ተጽዕኗቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ ኢ.ብ.ኮም ከመንግስት ተልዕኮ እንደተሰጠው እንዲሁም እንደ ቢዝነስ ተቋም ፋይናንስ ትልቅ ተጽዕኖን ፈጥሮበታል፡፡ ባለበት የፋይናንስ ችግር ምክንያት ያሉበትን ወጪዎች ለመሸፈን ከተልዕኮው ባፈነገጠ መልኩ ቢዝነስ ተኮር እና የተቋሙን ስታንዳርድ መጠበቅ እንዳይችል አድርጎታል፡፡ በቢዝነሱም በኩል ቢሆን የፋይናንስ ችግር ጥራት ያላቸውን ይዘቶች በማቅረብ ተወዳዳሪ እንዳይሆን

አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ኢ.ብ.ኮ ተልዕኮውን እንዲያሳካ እና በሚድያ ቢዝነስ ውስጥ ተወዳዳሪና ቀዳሚ ተመራጭ እንዲሆን በፋይናንስ ረገድ ችግሮቹን በመለየት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡

### 2.7 የአገልግሎት እና ሀብት አስተዳደር ማሻሻያ እንደመነሻ

ኢ.ብ.ኮ በርካታ በአግባቡ ሊመሩ የሚገባቸው ቋሚ፣ አላቂ እንዲሁም ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ሀብት ያለው መ/ቤት ነው፡፡ ለዓላማው መፈፀም ጋዜጠኛው በመላው ሀገራችን በመንቀሳቀስ የሚሠራባቸው መኪናዎች አሉት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአዲስ አበባና በመላው የሀገራችን አካባቢዎች የተለያዩ ህንፃዎችም አሉት፡፡ ከተባባሪ አካላት ጋር ውል ገብቶባቸው የሚሠሩ ኮንትራታዊ ሥራዎችም በስፋት አሉ፡፡

ኮርፖሬሽኑ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ግዥዎችንም የሚፈፅም በመሆኑ አደረጃጀቱ የሥራውን ስፋትና ሁሉን አቀፍ አገልግሎት መስጠት በሚያስችል መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ የነበረው አደረጃጀት መጣመር ያልነበረባቸውን እንደ ጠቅላላ አገልግሎት፣ ጋራዥና ትራንስፖርት የሥራ ክፍሎችን ጨፍልቆ ከማደራጀቱም በላይ የሥራ ክፍሉ አሟልቶ ይዞ ማደራጀት የሚገባቸው የኮንትራት አስተዳደርና የህንፃ አስተዳደር ክፍሎችን ይዞ አልተደራጀም፡፡ ኮርፖሬሽኑ ያለውን የንብረት ብዛትና የሥራ ስፋትን ባላገናዘበ ሁኔታ የንብረት አስተዳደርን በግዥ ሥር በቡድን ያደራጀ ነበር፡፡ ይህም ለኃሊፊነትና ተጠያቂነት (authority and responsibility) ሥራም የማይመች ከመሆኑም በተጨማሪ ከሥራው ስፋት አኳያ ዝቅ ብሎ መደራጀቱ ተገቢ አልነበረም፡፡

### 2.8 ምቹ የሥራ ከባቢ መፍጠር እንደመነሻ

የሥራ ከባቢ ምቹነት ለሠራተኛም ይሁን ለተቋም ውጤታማነት ወሳኝ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡ የኢ.ብ.ኮ ህንጻ ለሚዲያ አገልግሎት ተብሎ የተሠራ ካለመሆኑም ባሻገር ተቋሙ ብሄራዊ ሚዲያ ከመሆኑ አንጻር የሚጠበቅበትን ያህል አገልግሎት እንዲሰጥ አላስቻለውም፡፡ በመሆኑም ተቋሙን በአጭር ግዜ ወደ ምቹ የሥራ ከባቢ ለመቀየር እና በብሄራዊ ሚዲያ ደረጃ የሚመጥነው የሚዲያ ከባቢ እንዲኖረው ቅድሚያ በመስጠት በልዩ ትኩረት ይሠራል፡፡

## 2.9 የማስፈጸም አቅምና የሰው ሀብት ልማት ማሻሻያ እንደመነሻ

የሰው ሀብት ልማት ክፍል የተቋሙን ቁልፍ ሀብት ማለትም የተቋሙን አመራር እንደዚሁም መላውን ሠራተኛ ከቅጥር፣ ምልመላ፣ መረጣ፣ ስምሪት እስከ ስንብት ያለውን የሥራ ክንውን የሚሠራ ክፍል ነው፡፡ በተጨማሪ የሰው ሀብት ልማት ክፍል ከሥራው ስፋት፣ ፍጥነትና ቅልጥፍና መፈለግ አኳያ ጠንካራ አደረጃጀት፣ ብቁ የሰው ኃይል እንደዚሁም ሥራና ሠራተኛን በሚገባ የማገናኘት ኃላፊነት ያለበት ክፍል ነው፡፡ ይህን ተልዕኮውን እንዲወጣ በዋና ዋና የሰው ሀብት ልማት ችግሮችን የለዩ የሰው ሀብት ልማት ሥራ ይከናወናል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ውጫዊ ሁኔታ ዳሰሳ

### 3.1. ሀገራዊ ሁኔታ እንደመነሻ

ሰኔ 14/2013 ዓ.ም ተካሄዶ በነበረው 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ የመጀመሪያ ዙር ውጤት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጊዜያዊ የምርጫው ውጤትን ሐምሌ 3 ይፋ ማድረጉን ተከትሎ ገዥው ፓርቲ መንግስት መመስረት የሚያችለውን ድምፅ ማግኘቱን ምክንያት በማድረግ የኢ.ፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲ፣ በፀጥታ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ጉዳዮች የመንግስታቸው ቀጣይ ትኩረት ምን ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁም መልዕክት ያስተላለፉ ስለሆነ በ2014 በጀት አመት የሚዲያ የዘገባ ትኩረት ተብሎም የሚጠበቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በውጤቱም ከአሸናፊነት ይልቅ ኃላፊነት፣ ከድል አድራጊነት ይልቅ ታላቅ የሆነ ሀገራዊ አደራ እንዲያድርብን አድርጎናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጣይ ጊዜያት ብልጽግና በሚመሠርተው መንግሥት ውስጥ በአስፈጻሚው አካልም ሆነ በፍርድ ቤቶች፣ በሌሎችም የፌደራልና የክልል ተቋማት ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣ በዘንድሮው ምርጫ በኃላፊነትና በብቃት የተወዳደሩ የሕዝብ አለኝቶችን ከዚህ በፊት ካደረግነው በእጅጉ ከፍ ባለና አዎንታዊ ለውጥ በሚፈጥር መልኩ እንደሚካትቱ እንዲሁም ኢትዮጵያን ከሚወዱ አካላት ጋር ሁሉ በትብብር ለመሥራት እንዲሁም የፖለቲካ ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሆነው ለሀገርና ለሕዝባችን በሚጠቅሙ ማናቸውም የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመግባባት ለመሥራት ዝግጁዎች ነን ሲሉ መግለጻቸው የዲሞክራሲ ሥርዓትን የበለጠ ለማጠናከር ያላቸውን ዝግጁነት የሚያሳይ በመሆኑ ለኮርፖሬሽኑ የዘገባ ዕቅድ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው ሀገራችን እንድትበለጽግ በኢኮኖሚውም ሆነ በማኅበራዊና ፖለቲካ ዘርፎች ዘላቂ መሠረት የሚሆኑ፣ በፍጥነት የሚጠናቀቁ፣ ጥራታቸው የተጠበቁ፣ ከብክነት ነጻ የሆኑ እና የምንፈጥራቸውን ተቋማት መሸከም የሚችሉ ትውልድ ተሻጋሪ መሠረተ ልማቶችን መገንባት እንቀጥላለን ያሉ ሲሆን የተቋማት ግንባታ በጥቂት ግለሰቦችና ነጠላ ተቋማት ላይ ከማተኮር ባለፈ ሀገራችንን በጽኑ መሠረት ላይ የሚያቆሙ ጠንካራና ዘመን ተሻጋሪ ሥርዓት ለማጽናት የሚስችሉ ገለልተኛና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚያገለግሉ ተቋማትን መገንባት ላይ ትኩረት ይደረጋል፤ ይኼ ማሕቀፍ ከፌደራል እስከ ክልል የሚገኙ ተቋማትን የሚያካትት ይሆናል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም እንደ ሀገር የሚያስተሳስሩን የጋራ አመለካከቶችና የጋራ ትርክቶች ላይ ትኩረት እንደሚሰጥ እንዲሁም የሞራል ልዕልናና ግብረገባዊነት ችግር የመቅረፍ ኃላፊነት መንግሥትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ላይ ብቻ የሚጣል ሳይሆን ከግልና ከቤተሰብ ጀምሮ የሚሠራ ሥራ መሆኑን መልዕክት አስተላለፊዋል፡፡

የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለተግባራዊነቱ የጋራ ትጋት እንደሚያስፈልግ የገለፁት ጠ/ሚ/ሩ በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የበጋ ሰብሎችና ፍራፍሬዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት ከተጀመሩ አነስተኛ መስኖዎች ባለፈ፣ ዝናብ አጠርነት ለመዋጋት በቴክኖሎጂ አማካኝነት ደመናን ወደ ዝናብ የመቀየር ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ እንዲሁም አየር ንብረታችንን የሚያስተካክለውና የብዝኃ ዕጽዋትና የብዝኃ እንስሳት ሀብታችንን በእጅጉ ያሳድጋል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦች ጋር የተዋደደ ተፈጥሮአዊ መስህብ በመሆን የቱሪስት ፍስትን እንዲጨምርና ኢኮኖሚያችን መስፈንጠር እንዲችል መደላድል ይሆናል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግራችንን ለመቅረፍና ለዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች መቀላጠፍ ጉልህ አስተዋጽዖ ከሚያበረክቱ ፕሮጀክቶቻችን መካከል አንዱና ወሳኙ የሕዳሴ ግድብ ግንባታችን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ከግድብም፣ ከኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭነትም በላይ ነው። ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ባለፈ ዳግም የመነሣታችን ተምሳሌት ነው። በራስ ዐቅም የመቆም፣ በራስ ፍላጎት የመመራት፣ የሉዓላዊነታችን ምልክት፤ የሀገራዊ አንድነታችን ገመድ ነው። በቅርቡ ሁለተኛውን ዙር የውኃ ሙሌት እንደሚፈጸም በመግለጽ፣ በሕዳሴ ግድብ ላይ ፍትሐዊ ተጠቃሚነታችን

እንዲጠበቅልን እንጂ መቼም ቢሆን ሌሎች ሀገራትን የመጉዳት ፍላጎት ኖሮን አያውቅም ሲሉ አስታውቀዋል፡፡ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለንም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በጋራ ተጠቃሚነት ዙሪያ ለመሥራት ሁሌም ዝግጁዎች ነን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ሰላሙ እንዲጠበቅ፣ የጋራ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር፣ በትብብርና በመግባባት በጋራ ለማደግ ያላቸውን ፍላጎት ማስተላለፋቸው የኮርፖሬሽኑ የዲፕሎማሲ ዘገባ ዕቅድ እንደመነሻ መውሰድ ተችሏል፡፡

### 3.2. የፕሬዘዳንቷ ንግግር እንደመነሻ

የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ መክፈቻ ጉባኤ የተካሄደ ሲሆን በሁለቱም ምክር ቤቶች የመክፈቻ ስነ ስርዓት ላይ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ንግግር አድርገዋል፡፡

በንግግራቸው ባለፉት ዓመታት አብሮ መኖራችንን ለማናጋት ብዙ ተሰርቷል ብዙ ዋጋም ተከፍሏል፤ የዛ ትግልና ፅናት ድምር ደግሞ ለዛሬ አዲስ ምዕራፍ አብቅቶናል፤ ለዚህ ምዕራፍ ያበቁንን ዋጋ የከፈሉትን ሁሉንም ደግሞ ማስታወስ ተገቢ ነው ሲሉም ገልፀዋል፡፡

በ2013 የተካሄደው ምርጫ በበርካታ መለኪያዎች ካለፉት ዓመታት የተሻለ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ ባለፉት ሶስት ዓመት ሲወሰድ የነበረው የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ኢኮኖሚው ከነበረበት የቁልቁለት ጉዞ በመታደግ ከፍተኛ ውጤት አምጥቷል፤ ከሞላ ጎደልም ውጤታማ ነበሩ ብለዋል፡፡ነገር ግን የኑሮ ውድነትና ስራ አጥነት የኢኮኖሚው ፈተናዎች ሆነው ቀጥለዋል፡፡

ያለፈው አመት የህዳሴው ግድብ ሁለተኛ ዙር ሙሌት የተከናወነበት እንዲሁም ሌሎች ስኬቶች የተገኙበት አመት ነበር ያሉት ፕሬዚዳንቷ ዓመታቶቹ እንደ ሃገር ታላላቅ ስኬቶች ያስመዘገብንበት ቢሆንም አሳዛኝ ድርጊቶችም ተፈፅመዋል ነው ያሉት፡፡

በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ከሚንቀሳቀሱ አሸባሪዎች ጋርም በንጹሀን ላይ ግድያ ፈፅመዋል፣ ንብረት ወድሟል፣ መፈናቀል ሲፈጽሙ ቆይተዋል፤ በዚህም አሁን ህብረተሰቡ ወደ ቤት ንብረቱ እንዲመለስ እና በቶሎ እንዲያገግም ማድረግ ተጠናክሮ የሚቀጥሉ ጉዳዮች መሆናቸውን አመላክተዋል፡፡

በሌላ በኩልም በ2014 በጀት ዓመት የመንግስት ገቢን 600 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር ለማድረግ ታቅዷል ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 83 በመቶ የሚሆነውን ከታክስ ለመሰብሰብ መታቀዱን አመላክተዋል፡፡ጠቅላላ የሸቀጦች የውጭ ንግድ ገቢን ደግሞ 5 ነጥብ 25 ቢሊየን ዶላር ለማድረግ ታቅዷል፡፡

እንዲሁም በተያዘው በጀት ዓመት የውጭ ንግድና የውጭ ምንዛሬን እንዲያድግ ይሰራል፤ በከተሞች ባልተማከለ የከተማ አስተዳደር እንዲኖር ይደረጋል ብለዋል፡፡

ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘን ገቢ ለማሳደግም ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች ይጎለብታሉ፤ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች እንዲለሙ ይደረጋል፣የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት ክፍት ይሆናሉ ነው ያሉት፡፡

በአመፅና በጠመንጃ ትግል ወይም ንፁሃንን በማሻበር የሚገኝ ስልጣን ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ምድር እንደማይኖር ሊታወቅ ይገባል ሲሉ አፅንኦት የሰጡት ፕሬዚዳንቷ፤ ስልጣን ሰጪውም ስልጣን ነሺውም የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም በህጋዊ ምርጫ ላይ ብቻ በመሳተፍ ህዝባችሁን የምታገለግሉበት ሰላማዊ መንገድ እንድትከተሉ ሲሉ አሳስበዋል፡፡

በደም የተፃፈን ታሪክ ብዕር ቀለም አይለውጠውም ያሉት ፕሬዚዳንቷ ኢትዮጵያውያን በሃገራቸው ብሄራዊ ጥቅምና ልኡላዊነት ከማንም ጋር አንደራደርም ብለዋል ፡፡

ለዚህም የውጭ ግንኙነት መርህ የኢትጵያን ልዑላዊነት የሚያከብር፣ ብሄራዊ ጥቅማችንን እና ክብራችን በማያጓድል መልኩ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

ለቀጣይ ጎረቤት አገራትን ያስቀደመ የዉጭ ግንኙነት ፖሊሲ ቀርፀን እንሠራለን ነዉ ያሉት ፕሬዚዳንቷ፡፡

በምሥራቅ አፍሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ብዙ ፍላጎቶች የሚንፀባረቁ መሆኑን በመግለጽም፣ ኢትዮጵያ በቀጣናዋ የሚፈፀሙ ገዳዮችን ከሩቅ ሆና አትመለከትም ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ትሥሥር እና የጋራ ብልጽግናን መሠረት ያደረገ እንደሚሆን ገልጸዋል።

ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትም በዙሪያችን ያሉ ጎረቤት ሀገራትን ያስቀደመ ሆኖ እንደሚቀጥል እና በትብብር እና በመግባባት ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሚተገበር እንደሚሆንም አብራርተዋል።

### 3.3. የህልውና ዘመቻው እንደ መነሻ

ሀገራችን ተገዳ የገባችበት ህልውና የማስከበር ዘመቻ በ2014 ዓ.ም አንኳር ጉዳይ ነው፡፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ጠላቶቿ በመተባበር ሀገር የማፍረስ ሴራቸውን ለመተግበር ሌት ከቀን የተጉበት ወቅት ነው፡፡መንግስትና ህዝብ በመተባበር፣ በመደማመጥና ከደጀን እስከ ግንባር መስዋዕትነት ድረስ የነበረው የተቀናጀ ሀገርን የማዳን የህልውና ዘመቻ ጠላቶቻችን ባሰቡት ልክ እንደማይሳካላቸው ያረጋገጠ ነው፡፡ የምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን በሀት የተፈበረከ ፕሮፓጋንዳቸው በዲያስፖራው ማህበረሰብ ቁራጥ ተጋድሎ መመከቱና እንዲሁም በሀገር ውሰጥ ይቀርቡ የነበሩ የእውነታ ዘገባዎች አመርቂ ውጤት አምጥተዋል፡፡ የህልውና ዘመቻው በቀጣይም በሁሉም ዘርፍ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ኢ.ብ.ኮ ከሚዲያ አንጻር የሚጠበቁበት የቤት ስራዎች መኖራቸውን ከግንዛቤ በማስገባት የህልውና ዘመቻው ዘገባዎች እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

### 3.4. በሚዲያ ኢንዱስትሪ የተፈጠረ ውድድር እንደመነሻ

እንደ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን መረጃ መሰረት ባለፉት ጥቂት አመታት በሀገራችን የሕዝብ ንግድ እና የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች ቁጥር በፍጥነት እያደገ ይገኛል፡ ፡ በመረጃው መሰረት በአሁኑ ጊዜ በአስራ ሁለት (12) የህዝብ ቴሌቪዥን፣ አስራ ዘጠኝ (19) የንግድ ቴሌቪዥን፣ አንድ (1) የማህበረሰብ ቴሌቪዥን፣ ስምንት (8) የንግድ ሬዲዮ፣ ሰላሳ አንድ (31) ማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ በስርጭት ላይ ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ ጣቢያዎች የይዘት ትኩረት ሲታይ የንግድ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያዎች የፋይናንስ ግብዓት እጥረት እንዳያጋጥማቸው ሰፊ የአየር ሰዓታቸው ለመዝናኛ ዝግጅቶችና ፕሮግራሞች የሚያውሉ እና በመዝናኛ ፕሮግራም ተወዳጅነትን ያተረፉ ናቸው፡፡ በሀገራችን ስፖርት፣ ሙዚቃ፣ ፊልምና ድራማ ይዘትን ብቻ የሚያስተላለፉ የሳተላይት ጣቢያዎችም ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ አንዳንዱ በዘርፉ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ለመዝናኛ ሾዎች ለስቱዲዮ ግንባታ፣ ለፕሮግራም አቅራቢ፣ ለሜካፕና አልባሳት ወጪ

ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ያደርጋሉ፡፡ በማስታወቂያና ስፖንሰርሺፕ ያላቸው የገበያ ድርሻ የሚናቅ አይደለም፡፡

የሕዝብና የማህበረሰብ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ የሚባሉት ደግሞ ባለቤትነታቸው በብዛት ለክልል መንግስታ ሲሆን ትኩረታቸው ገቢን ማመንጨት ሳይሆን ማኅበረሰቡ መረጃዎችን እንዲያገኙ፣ ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ ዕሴቶቻቸውንና የጥበብ ሥራዎቻቸውን እንዲያጎለብቱ፣ በአካባቢያቸው ልማት፣ ሰላም፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት አድርገው ይሰራሉ፡፡

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በ2014 በጀት አመት የሚያከናውናቸው የይዘት፣ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ ልማት፣ የብራንዲንግና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች በመዝናኛ ፕሮግራሞች ከንግድ ጣቢያዎች፣ በዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ከሕዝብና ማህብረሰብ ጣቢያዎች ጠንካራ ውድድር መኖሩ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የኢ.ብ.ኮ ስትራተጂካዊ ዕቅድ

### 4.1. የኮርፖሬሽኑ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች

**የትኩረት መስክ** 1፡ የአሠራር ስርዓትና የሕግ ማሻሻያ

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** ቀልጣፋ አገልግሎት

**የትኩረት መስክ** 2፡ የላቀ ይዘት

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** የአድማጭ ተመልካች እርካታ

**የትኩረት መስክ** 3፡ ተደራሽ ዲጂታል ሚዲያ

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** የላቀ ተደራሽነት

**የትኩረት መስክ** 4፡ የዘመነ ቴክኖሎጂ

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** ጥራትና ተደራሽነት

**የትኩረት መስክ** 5፡ ፋይናንስ

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** የተሻለ የፋይናንስ አቅም

**የትኩረት መስክ** 6፡ የገበያ ልማትና ብራንዲንግ

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** የላቀ ሀብት

**የትኩረት መስክ** 7፡ ምቹ የስራ ቦታ

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** የላቀ አገልግሎት

**የትኩረት መስክ 8፡** የማህበራዊና በጎ አድራጎት አገልግሎት

**የትኩረት መስኩ ውጤት፡** ውጤታማ ማህበራዊ ኃላፊነት

**ሠንጠረዥ 5፡- ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች መግለጫ**

| ተ.ቁ | የትኩረት መስክ | የትኩረት መስክ መግለጫ | የትኩረት መስክ ውጤቶች |
|---|---|---|---|
| 1. | **የአሠራር ስርዓትና የሕግ ማሻሻያ** | ፈጣን ውሳኔ መስጠት የሚያስችሉ አሰራሮች የሚተገብር፣ የኢ.ብ.ኮን ተልዕኮ ለማሳካት በሚያስችሉ ህጎች የተደገፈ፣ የነባሩን መዋቅር ችግሮች የቀረፈና ሥራና ሰራተኛን ያገናኘ ተቋም መፍጠር ማለት ነው፡፡ | ቀልጣፋ አገልግሎት |
| 2. | **የላቀ ይዘት** | ትክክለኛና ፈጣን መረጃ በማቅረብ ቀዳሚ የሆነ፣ ተመራጭ ሚዲያ ሆኖ ለሀገር ግንባታ አስተዋጽኦ ማበርከት ማለት ነው፡፡ | የአድማጭ ተመልካች እርካታ |
| 3. | **ተደራሽ ዲጂታል ሚዲያ** | ተወዳጅና ተመራጭ፣የዘርፉን ውድድር በበላይነት የሚመራ፣ዓለም አቀፍ ተከታዮችን በብዛት ያፈራ፣ የገቢ አቅሙን ያጎለበተ ዘርፍ ማድረግ ማለት ነው፡፡ | የላቀ ተደራሽነት |
| 4. | **የዘመነ ቴክኖሎጂ** | በየጊዜው ከሚዘምነው የሚዲያ ቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር የሚጓዝ፣ ቀላልና ፈጣን የስርጭት አማራጮችን በመጠቀም ይዘትን በጥራት ተደራሽ የሚያደርግና በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን የታገዘ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ማለት ነው፡፡ | ጥራትና ተደራሽነት |
| 5. | **ፋይናንስ** | የውስጥ ገቢ አሰባሰብን ያዘመነ፣ የዱቤ አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን የቀረፈ፣ የሀብት ብክነትን የተከላከለ አሰራር መተግበር ማለት ነው፡፡ | የተሻለ የፋይናንስ አቅም |
| 6. | **የገብያ ልማትና ብራንዲንግ** | ዘመናዊ የገበያ አሰራሮችን የሚተገብር፣ ልቆ የወጣ የገበያ ተወዳዳሪነት ያለው ፣ ተለዋዋጭ የገበያ መንገዶችን በመተግበር የተቋሙን የገቢ መጠን አስተማማኝ ማድረግ ማለት ነው፡፡ | የላቀ ሀብት |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስክ | የትኩረት መስክ መግለጫ | የትኩረት መስክ ውጤቶች |
|---|---|---|---|
| 7. | **ምቹ የሥራ ቦታ** | ለሰራተኛው ለስራ ምቹ የሆነ ህንጻ ባለቤት የሆነ፣ ዘመናዊና አለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ስቱዲዮች የገነባ፣በሚዲያው ዘርፍ ቀዳሚ የሆነ ምቹ ተቋም ማድረግ ማለት ነው፡፡ | የላቀ አገልግሎት |
| 8. | **የማህበራዊና በጎ አድራጎት አገልግሎት** | በአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተካላ ተሳትፎ በማድረግ፣የተቋሙ ሴቶች አቅም የሚያሳዱጉ አጫጭርና ረዥም የሙያ ስልጠና በመስጠት፣በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በበጎ ስራቸው ለሚታወቁ ተቋማትና ግለሰቦች የነጻ ማስታወቂያና ፕሮግራሞች በማስተላለፍ፣ ሰው ለጠፋባቸው አፋልጉኝ የሬዲዮ ማስታወቂያ በነጻ ማስተላለፍ፣ ወላጆቻቸውን በኤች አይቪ/ኤድስ ያጡ እና ለችግር የተጋለጡ 9 (ዘጠኝ) ታዳጊዎች በቋሚነት የሚደረግ ድጋፍ አጠናክሮ ማስቀጠል፣ በጦርነቱ ለተፈናቀሉና ለመከላከያ ሠራዊት ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ | ውጤታማ ማህበራዊ ኃላፊነት |

## 4.2. ግቦች፣ ዝርዝር ተግባራት እና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

**ግብ 1፡- የአሠራር ስርዓትና የሕግ ማሻሻያ**

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- መልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻል፣
- የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች ማሻሻል፣
- የመዋቅር ማሻሻያ መስራት፣

**የአፈጻጸም አቅጣጫዎች**

- የመልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ እንዲጸድቅ ለተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፣
- ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎችን ከሪፎርሙ አንጻር ማሻሻል፣
- የነባሩ መዋቅር ችሮችን በሚቀርፍ የመዋቅር ማሻሻያ መስራት፣
- ሥራን እና ውሳኔ ሰጪነትን በሚያቀላጥፍ የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ፣
- ያለውን የሰው ኃይል በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ማሻሻያ ማድረግ፣

**ግብ 2፡- የላቀ የይዘት አሰራር ማሳደግ**

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- በየደረጃው የሚደረጉ የኤዲቶሪያል ውይይቶችን ማጠናከር፣
- የቅድመ እና ድህረ ፕሮዳክሽን አሰራሮችን ማጠናከር፣
- ይዘቶች ፎርማታቸውን ጠብቀው እንዲቀርቡ ማድረግ ፣
- አዳዲስ ፎርማቶችን ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የሜክአፕ፣ የአልባሳት፣ የግራፊክስና የፈጠራ አጠቃቀም ማጠናከር፣
- የአድማጭ ተመልካች ግብረመልስ ትንተና ስርዓት ማጠናከር፣
- የኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ፖሊስ ማሻሻያ ማከናወን፣

**የአፈጻጸም አቅጣጫዎች**

- የመንግስት ክዋኔ ዘገባዎችን መቀነስ፣
- ኢ.ብ.ኮን ዜና ሠባሪ (news breaker) ማድረግ፣
- ከሀርድ ዜናዎች (ፖለቲካ) በተጨማሪ ሶፍት ዜናዎችን (አዝናኝ) ማካተት፣

- የዜና ፎርማቶችን ማስተካከልና ከስማቸው ጀምሮ ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የስቱዲዮና ግራፊክስ ማሻሻያ መስራት፣
- አዳዲስ የጋዜጠኞችን አቀራረብ ማስተዋወቅ፣

**ግብ 3፡- የዲጂታል ሚዲያን እና የሌሎች ስርጭቶች ተደራሽነትን ማሳደግ**

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- የሞባይል አፕሊኬሽን እና የኮርሬሽኑን ዌብሳይት ሥራ ማስጀመር፣
- የስቱዲዮ የውስጥ ዲዛይን ማሻሻያ (Interior Design) ስራዎች ማከናወን፣
- የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን አርካይቭ ለስራ ምቹ ማድረግ፣
- ዘመናዊ የቀረፃ እና ስርጭት አሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- የቀጥታ ስርጭት አሰራርን ማዘመን እንዲሁም መዘርጋት፣
- የተጨማሪ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ስቱዲዮዎች መገንባት፣
- ስርጭት የተቋረጠባቸው (ሀረር) ስቱዲዮ ሥራ ማስጀመር፣
- የኒው ሚዲያና ኔትወርክ መሰረተ ልማት ማስፋፋትና ማሻሻል፣
- ኤፍ ኤም ትራንስሚተር የማስፋፊያ ስራዎችን ማከናወን፣
- የስርጭት ሽፋንን ለመጨመር በጣም ቀላል የሆኑ የዲኤምኤንጂ (DMNG) ሞባይል ሲስተሞችን መግዛት፣
- የተጀመረውን የኤሲ እና ፓዎር ሲስተም (AC and Power System) መትከል፣ የሳተላይት ሲስተም አፕግሬድ ማሻሻያ ግዥ ማከናወን፣የቀጥታ ስርጭት ኦቢቫን ጥገና እና የተሸከርካሪ ግዢ ማከናወን፣

**የአፈጻጸም አቅጣጫዎች**

- በዞን ስቱዲዮዎች እና በማሰራጫ ጣቢያ ትራንስሚተሮች ላይ የሚያጋጥሙ ብልሽቶችን እና አስተዳደራዊ ችግሮችን ለመፍታት ሰፊ ስምሪት ማከናወን እንዲሁም በየጣቢያው ያሉ ባለሙያዎችን አቅም ማሳደግ፣
- በ2013 ዓ.ም በግዥ ሂደት ላይ ያሉትን በማጠናቀቅ የተበላሹትን በርካታ የቴክኖሎጂ ዕቃዎች ጥገና፣ ተከላና ማሻሻያ ስራ ማከናወን፣

- ለቴሌቪዥን ዲጂታላይዜሽን ግንባታ ማስፈጸሚ እንዲሁም በሌሎች ለስቱዲዮና ትራንስሚተር ማሻሻያ ስራ የሚሆን የካፒታል በጀት ከመንግስት ድጋፍ እንዲሰጥ ማድረግ፣
- በኃይልና ኔትወርክ ጋር የተያያዙ ችግሮች ከኢትዮ ቴሌኮም እና ከመብራት አገልግሎት የበላይ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ዘላቂነት መፍትሔት እንዲሰጥ ክትትል ማድረግ፣

## ግብ 4፡- ዘመናዊ የሚዲያ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሻሻል

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ የባለሙያዎችን አቅም ማሳድግ፣
- የስቱዲዮች ጥገና እና ማሻሻያ ማድረግ፣
- የማቀዝቀዣና ፓወር ሲስተም ችግርን መፍታት፣
- ኔትዎርክ መሰረተ ልማት አቅምን ማሳደግ፣
- የኦቢ ቫን እና ሌሎች የመለዋወጫ እቃዎች ግዥዎችን ማካሄድ፣
- የቪዲዮ ዎል ግንባታ ማካሄድ፣

## የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

- ከቴክኖሎጂ እና ከስልጠና ማዕከል ባለሙያዎችን በማቀናጀት ጥናት እንዲያካሂዱና ችግሮችን እንዲለዩ ማድረግ፣
- የሳተላይት ስርጭትን ከSD ሙሉ በሙሉ ወደ HD ማሻሻል፣

## ግብ 5፡- የፋይናንስ አቅም ማሳደግ

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- ከማስታወቂያ ሽያጭና ስፖንሰርሺፕ፣ ከሀብት ኪራይ እና በሁነት ዝግጅት ብር 700 ሚሊዮን ሽያጭ ማከናወን፣
- ከዱቤ ገቢ ብር 500 ሚሊዮን መሰብሰበብ፣
- ከዋጋ መቀበያ ገቢ ብር 40,000,000.00 ገቢ ማስገኘት፣
- ከዲጂታል ገበያ (ዩቲዩብ) 100,000.00 የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት፣

### የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

- ዘላቂ የገበያ ልማት እና የፋይናንስ አመራጭ ስትራቴጂ በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከአሁን በፊት ከኮርፖሬሽኑ ጋር በማስታወቂያ፣ በስፖንሰርሺፕ እና በአየር ሰዓት ኪራይ በትብብር የሚሰሩ ተቋማት የሚጋ ፕሮጀክት ስምምነት በማስቀጠል እንዲሁም አዳዲስ የመግባቢያ ስምምነት መፈራረም፤
- የ2013 ዓ.ም አፈጻጸም መነሻ በማድረግ የሽያጭ አርዕስቶች የገቢ የእቅድ ድርሻ ላይ መጠነኛ ማሻሻያዎችን በማድረግ የቴሌቪዥን ማስታወቂያና ስፖንሰርሺፕ የእቅዱን 50%፣ የህብት ኪራይ 30%፣ የሬዲዮ ማስታወቂያና ስፖንሰርሺፕ 12% እንዲሁም የሁነት ፈጠራና ፕሮጀክት  8% እንዲሆን በማድረግ ጠንካራ የገበያ ማፈላለጊ ስራ ማከናወን፡፡ በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ቻናል የአመቱ የሚጠበቅበትን የገቢ ዕቅድ በመለየት መስራት፣
- ሚዲየሞችን በማቀናጀት የፓኬጅ ሽያጭ ማከናወን፣
- የዱቤ ክትትል በማድረግ እስከ 2013 ያልተሰበሰበውን ዕዳ መሰብሰብ፣ የ2014 በጀት ዓመት በውል መሰረት እንዲሄድ ክትትል ማድረግ፣
- መሰብሰብ የማይችሉትን ዕዳዎች በመለየት በተቋማቱ ላይ በውሉ መሰረት በሕግ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣
- የቴሌቪዥን ባለቤትነት አመታዊ ክፍያ በኮሚሽን ስርዓት ሰፊ ማህበራትን በማሰራት እንዲሁም የቴሌቪዥን ባለቤትነት አመታዊ ክፍያ ማሻሻያ ስራ ማጠናቀቅ፣

### ግብ 6፡- የገብያ ልማትና ብራንዲንግ

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ኢ.ብ.ኮን በደንብ ማስተዋወቅ፣
- ደረጃውን የጠበቀ የታዳሚያን ዓይነትና ፍላጎት ጥናት ማካሄድ፣
- የብራንድ አስተዳደርን ማሻሻልና ማጠናከር፣

**የአፈጻጸም አቅጣጫዎች**

- የጥናት ግብዓቱን ለፕሮግራም ዝግጅት መጠቀም፣
- ተፎካካሪ ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን ተከታትሎ በማጥናት ፕሮግራሞችን ማስተካከል፣
- የገበያ ልማት አስተዳደር የሚያተጉ ዕቅዶችን ማስቀመጥ፣ስኬትን ማበረታታት፣

**ግብ 7፡- ምቹ የስራ አከባቢን በመፍጠር የሰራተኛ እርካታን ማሳደግ**

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ወደ ሸጎሌ አዲሱ የኢ.ብ.ኮ ህንጻ መዛወር፣
- የሚዲያ ኮምፕሌክስ ዲዛይን ማሰራት፣
- የቢሮ ቁሳቁስ በአዲስ ማሟለት፣
- የኮርፖሬሽኑ ህፃናት ማቆያ ማዕከል አገልግሎትን ለወላጆች ምቹ ማድረግ፣
- የሰራተኛ ካፍቴሪያ  በጥራት አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- የስልጠና ማዕከል ግቢ የማስዋብ ሥራ ማከናወን፣

**የአፈጻጸም አቅጣጫ**

- ለሚዲያ ተስማሚ የሆነ የቢሮ አደረጃጀት ለውጥ ማድረግ፣

**ግብ 8 ፡- በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የበጎ ተግባራት ተሳትፎ ማሳደግ**

ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተካላ ፕሮግራም እና በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳትፎ ማድረግ፣
- በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በበጎ ስራቸው ለሚታወቁ ተቋማትና ግለሰቦች የነጻ ማስታወቂያና ፕሮግራሞች ማስተላለፍ
- ሰው ለጠፋባቸው አፋልጉኝ የሬዲዮ ማስታወቂያ በነጻ ማስተላለፍ
- የፀረ-ፆታ ጥቃት ቀን፣ ዓለም አቀፍ የፀረ-ኤድስ ቀን፣ ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ምክንያት በማድረግ የንቅናቄ እና ግንዛቤ ሥራዎች ማከናወን

- የተቋሙ ሴቶች አቅም የሚያሳዱጉ አጫጭርና ረዥም የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ
- ወላጆቻቸውን በኤችአይቪ/ኤድስ ያጡ እና ለችግር የተጋለጡ 9 (ዘጠኝ) ታዳጊዎች በቋሚነት የሚደረግ ድጋፍ ማጠናከር
- ብቃትን መሰረት በማድረግ ሴቶችን ወደ አመራር የማምጣት ስራ መስራት
- አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ኮንቨንሽኖችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ቀጥታ ስርጭት መስማት ለተሳናቸው ተደራሽ ለማድረግ በምልክት ቋንቋ ማስተላለፍ፣
- በጦርነት ለተፈናቀሉና ለመከላከያ ሠራዊት ድጋፍ ማድረግ፣

## የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

- በሴቶች፣ በሕፃናትና አካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማትን ጋር በመተባበር የአይነትና የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብ፣
- ከሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች የበጎ አድራጎት አመታዊ መዋጮ ክፍያ እና የአይነት ድጋፍ ማሰባሰብ፣

## ሠንጠረዥ 6፡- ተቋማዊ የ2014 ዓ.ም ግቦች፣ መለኪያዎች እና ኢላማዎች

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራት | የተግባራት ክብደት | መለኪያዎች | የ2013ዓ.ም አፈጻጸም | የ2014ዓም ዒላማ | የሩብ ዓመት እቅድ | | | | በጀት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | |
| 1 | የአሠራር ስርዓትና የሕግ ማሻሻያ ማካሄድ | 5 | 1.1 የአዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ ለተወካዮች ም/ቤት ማቅረብ | 3 | ቁጥር | ---- | 1 | | X | | | |
| | | | 1.2 የመዋቅር ማሻሻያ መስራት | 2 | ቁጥር | ---- | 1 | | X | | | |
| 2 | የአድማጭ-ተመልካች እርካታና አመኔታ ማሳደግ | 18 | 2.1 የአድማጭ-ተመልካች አመኔታና እርካታ ደረጃ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | 8 | የተከናወኑ የደሰሳ ጥናቶች | 1 | 2 | | X | | X | |
| | | | 2.2 በየሚዲየሙና በየፕሮግራሙ የአድማጭ ተመልካች ቁጥር ማሳደግ | 10 | የጨመረ የማህበራዊ ትሰስር ገጽ ተጠቃሚዎች ቁጥር በሚሊዮን | 7 | 10 | 0.5 | 0.5 | 1 | 1 | |
| 3 | የሥርጭት ተደራሽነትና ጥራት ማሳደግ | 15 | 3.1 የሞባይል አፕሊኬሽን እና የኮርፖሬሽኑን ዌብሳይት ሥራ | 8 | የተከናወኑ ሥራዎች | | 2 | | X | | | |

## ሠንጠረዥ 6፡- ተቋማዊ የ2014 ዓ.ም ግቦች፣ መለኪያዎች እና ኢላማዎች

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራት | የተግባራት ክብደት | መለኪያዎች | የ2013ዓ.ም አፈጻጸም | የ2014ዓም ዒላማ | የሩብ ዓመት እቅድ | | | | በጀት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | |
| | | | ማስጀመር | | | | | | | | | |
| | | | 3.2 የስቱዲዮ የውስጥ ዲዛይን ማሻሻያ (Interior Design) እና አዲስ ስቱዲዮ ግንባታ | 7 | ዲዛይናቸው የተሻሻሉ(አዲስ የተገነቡ) ስቱዲዮች | 6 | 10 | | 3 | 7 | | 130 ሚሊዮን ብር |
| 4 | ዘመናዊ የሚዲያ ቴክኖሎጂ መጠቀም | 7 | 4.1 በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ የባለሙያዎችን አቅም ማሳድግ<br><br>4.2 ዘመናዊ የአይሲቲ መሳሪያዎች ማሟላት | 4<br><br>3 | አጫጭር የሥራ ላይ ስልጠና የተሰጣቸው ባለሙያዎች ብዛት በቁጥር<br>ለአይሲቲ መሳሪያዎች ግዢ የተያዘ በጀት በሚሊዮን ብር | | 30<br><br>20 | 5 | <br><br>X | 10 | 5 | |
| 5 | ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም | 35 | 5.1 የተሰበሰበ ዱቤና ዕለታዊ የሽያጭ ገቢ | 10 | የተሰበሰበ ገቢ ሪፖርት በብር | 450 ሚሊዮን | 700 ሚሊዮን | 100ሚሊን | 150 ሚሊን | 200 ሚሊዮን | 250 ሚሊዮን | |

ሠንጠረዥ 6፡- ተቋማዊ የ2014 ዓ.ም ግቦች፣ መለኪያዎች እና ኢላማዎች

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራት | የተግባራት ክብደት | መለኪያዎች | የ2013ዓ.ም አፈጻጸም | የ2014ዓም ኢላማ | የሩብ ዓመት እቅድ | | | | በጀት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | |
| | ና የፋይናንስ አቅምን ማሳደግ | | 5.2 የተሌቪዥን ባለቤትነት ገቢን በትኩረት መሰብሰብ | 2 | የተሰበሰበ የቴሌቪዥን ባለቤትነት ገቢ | | 40 ሚሊዮን | 10 ሚሊዮን | 10 ሚሊዮን | 10 ሚሊዮን | 10 ሚሊዮን | |
| | | | 5.3 ከዩቲዩብ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ | 3 | የተሰበሰበ የዩቲዩቭ ገቢ በአሜሪካ ዶላር | | 100 ሺ.ህ ዶላር | 25ሺ.ህ ዶላር | 25ሺ.ህ ዶላር | 25ሺ.ህ ዶላር | 25ሺ.ህ ዶላር | |
| | | | 5.4 በጀትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ በላቀ ደረጃ መጠቀም | 10 | በቁጠባ ሥራ ላይ የዋለ በጀት በመቶኛ | 90 | 100 | X | X | X | X | 1.5 ቢሊዮን ከመንግስት የተመደበ |
| | | | 5.5 የውጭና የውስጥ ኦዲት ግኝቶች እንዲሁም የአሰራር ስርዓት ጥናት ውጤት መሰረት | 10 | በኦዲት ግኝት የተስተካከሉ አሰራሮች በመቶኛ | | 100 | X | X | X | X | |

## ሠንጠረዥ 6፡- ተቋማዊ የ2014 ዓ.ም ግቦች፣ መለኪያዎች እና ኢላማዎች

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራት | የተግባራት ክብደት | መለኪያዎች | የ2013ዓ.ም አፈጻጸም | የ2014ዓም ኢላማ | የሩብ ዓመት እቅድ | | | | በጀት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | |
| | | | የማሻሻያ አሰራር መተግበር | | | | | | | | | |
| 6 | ገበያ ልማትና ብራንዲንግ | 5 | 5.1ከገበያ ልማት የተገኘ የሽያጭ | 5 | የሽያጭ ሪፖርት በብር | 500ሚ ሊዮን | 700ሚ ሊዮን | 150ሚ | 150ሚ | 200ሚ | 200ሚ | |
| 7 | ምቹ የስራ አከባቢን በመፍጠር የሰራተኛ እርካታን ማሳደግ | 5 | 5.1 ለሥራ ተስማሚ የሆነ ቢሮ ማመቻቸት፣የስራ መሳሪያዎች ማመሟላት፣ የማበረታቻ ሥርዓት ማመቻቸት | 5 | የተመቻቼ የስራ ቦታና የሰራተኞች እርካታ በመቶኛ | | 100 | X | X | X | X | |
| 8 | በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የበጎ ተግባራት ተሳትፎ ማሳደግ | 10 | 8.1 በአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተካላ ፕሮግራም እና በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳትፎ ማድረግ | 2 | በችግኝ ተከላና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት መሳተፍ | | 1 ጊዜ | X | | | | |
| | | | 8.2 ሰው ለጠፋባቸው አፋልጉኝ የሬዲዮ | 2 | የሚነገሩ ማስታወቂያዎች | | 50 ሺ.ህ ብር | X | X | X | X | |

## ሠንጠረዥ 6፡- ተቋማዊ የ2014 ዓ.ም ግቦች፣ መለኪያዎች እና ኢላማዎች

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራት | የተግባራት ክብደት | መለኪያዎች | የ2013ዓ.ም አፈጻጸም | የ2014ዓም ዒላማ | የሩብ ዓመት እቅድ | | | | በጀት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | |
| | | | ማስታወቂያ በነጻ ማስተላለፍ | | | | | | | | | |
| | | | 8.3 የተቋሙ ሴቶች አቅም የሚያሳዱጉ አጫጭርና ረዥም የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ | 3 | በስልጠና የተሳተፉ የሴት ሠራተኞች በቁጥር | | 200 | | X | X | X | |
| | | | 8.4 ወላጆቻቸውን በኤችአይቪ/ኤድስ ያጡ 9 ታዳጊዎች በቋሚነት የሚደረግ ድጋፍ ማጠናከር | 1 | ለህጻናቱ የሚደረግ ድጋፍ በብር | | 100 ሺ.ህ ብር | 25ሺ.ህ ብር | 25ሺ.ህ ብር | 25ሺ.ህ ብር | 25ሺ.ህ ብር | |
| | | | 8.5 በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በበጎ ስራቸው ለሚታወቁ ተቋማትና ግለሰቦች የነጻ | 2 | ለበጎ አድራጎት የተነገሩ ማስታወቂያዎች በብር | | 25 ሚሊዮን | X | X | X | X | |

ሠንጠረዥ 6፡- ተቋማዊ የ2014 ዓ.ም ግቦች፣ መለኪያዎች እና ኢላማዎች

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራት | የተግባራት ክብደት | መለኪያዎች | የ2013ዓ.ም አፈጻጸም | የ2014ዓም ኢላማ | የሩብ ዓመት እቅድ | | | | በጀት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | |
| | | | ማስታወቂያና ፕሮግራሞች ማስተላለፍ | | | | | | | | | |

# ምዕራፍ አምስት

## የድጋፍና ክትትል ስርዓት እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

### 5.1. የድጋፍና ክትትል ስርዓት

የዕቅዱ የድጋፍና የክትትል አግባብ እያንዳንዱ የሥራ ክፍልና ፈፃሚ ኃይል ከተቋሙ የሪፎርም 100 ቀናት ዕቅድ የተቀዳና የየሥራ ክፍሉን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ዕቅዱን እንዲከልስ ይደረጋል፡፡ ጠንካራ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት ለመፍጠር የሚያስችሉ፡-

- የግብረ-መልስ ስርዓትን መዘርጋት፤
- የማኔጅመንት እና የንዑስ ማኔጅመንት ስብሰባዎች ሳይቆራረጡ እንዲካሄዱ ማድረግ፤
- ከሚኒ ማኔጅመንት ስብሰባዎች የሚገኙ ግብአቶችን የተግባራዊ ማድረግ
- የዕቅድ አፈፃፀምን እየገመገሙ ያጋጠሙ ችግሮችን መፍታትና ጠንካራ ጎኖች ደግሞ ይበልጥ የሚጠናከሩበት መንገድ ማመቻቸት፤
- በየወሩ፣ በሩብ፣ በስድስት ወርና በዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀምን የሚገመግም የአመራር መድረክ ማካሄድ፤
- በየዘርፉ የሚካሄዱ ስብሰባዎች በዕቅድ አፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችንና ቅሬታዎችን መፍታት የሚያስችል ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤
- በሥራ አፈፃፀማቸው ውጤታማ የሆኑ ሠራተኞችን የማበረታቻ ስርዓት በመፍጠር ዕውቅና መስጠት የሚያስችል አሠራር መቅረፅና መተግበር፣
- ለኢ.ብ.ኮ ስራ አመራር ቦርድና ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት በማቅረብ አፈፃፀሙ እንዲገመገም ማድረግ፡፡ በዋናነት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡

### 5.2. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

#### ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

- የሀገሪቱ የፀጥታ ችግር በተቋሙ የገቢ አሰባሰብ ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

- በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት የግብዓት እጥረትና የአቅርቦት ሂደቱ የመጓተት ችግር ሊከሰት ይችላል፣
- የይዘት ክለሳውን ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ የሰው ኃይልና የማቴሪያል ግብዓት ፍላጎት ሊያጋጥም ይችላል፣
- የመብራት ኃይል እና የቴሌ መቆራረጥ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላል፡፡

**የመፍትሄ አቅጣጫዎች**

- ችግሮችን ተቋቁሞ በዕቅዱ የያዝናቸውን የይዘት እና የገቢ እቅዶች ለማሳካት የሚያስችል ስትራቴጂ በመቀየስ መስራት፤
- የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት በልዩ ሁኔታ ማግኘት እንዲቻል መንግስት ድጋፍ የሚያደርግበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተወያይቶ ማስወሰን፣ የዩቱዩብ ገቢ ለማሳደግ በዲጂታል ማርኬቲንግ ስራ በትኩረት ማከናወን እና ከግል ባንኮች የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበትን አማራጭ መሞከር፤
- በአጠቃላይ የአመራሩና ሰራተኛ የስራ ባህል እንዲሻሻል ማድረግ እና በሀገር ውስጥ የሚገኙ ግብአቶችን መጠቀም፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይት በማካሄድ የኤሌክትሪክ እና ቴሌኮም መቆራረጥ ችግር የሚፈታበት መንገድማመቻቸት፣

ሠንጠረዥ 7፡- የኢ.ብ.ኮ ሪፎርሙን ማስፈጸሚያ በጀት ዝርዝር

| ተ.ቁ | መደበኛ በጀት ደጋፍ | አስፈላጊው የብር መጠን |
|---|---|---|
| 1 | ለስምንት ወር ደመወዝ | 366,000,000.00 |
| 2 | ለሥራ ማስኬጃ የሚውል | 134,000,000.00 |
| | ድምር | 500,000,000.00 |

| ተ.ቁ | ለውጥ የሚደረገባቸው መስኮች | አስፈላጊው የብር መጠን |
|---|---|---|
| ለሬዲዮና ቴሌቪዥን ስቱዲዮ መጠባበቂያ ግንባታ | | |
| 1 | ለሬዲዮ ስቱዲዮ ግንባታ | 50,000,000 |
| 2 | ለቴሌቪዥን ስቱዲዮ | 80,000,000 |
| የቴክኖሎጂ ግዢ | | |
| 3 | ለሳተላይት መሳሪያዎች ግዢ | 40,000,000 |
| 4 | ለ78 በላይ የቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያዎች ለ40 በይ የብሔራዊ ሬዲዮ እና የኤፍ ኤም ማሰራጫ ጣቢያዎች የመለዋወጫ መሳሪያዎች ግዢ | 50,000,600 |
| 5 | ለስቱዲዮ መሳሪያዎች መለዋወጫ ግዢ | 60,000,000 |
| 6 | ለአይ ሲ ቲ መሳሪያዎች ግዥ | 20,000,000 |
| 7 | ፊልድ ካሜራ ግዥ | 70,000,000 |
| 8 | ለኤች ዲ ኦቪቫን ግዢ | 320,000,000 |
| 9 | ለቴሌቪዥን እና ሬዲዮ አርካይቭ ደረጃ ማሳደግና ማስፋፋት | 90,000,000 |
| የህንጻውን ዲዛይን ለማሻሻልና የኢንተሪየር ሥራ ከአንደኛ ፎቅ እስከ አሥራ ሦስተኛ ፎቅ ድረስ ለማሻሻል፡፡ | | |
| 10 | ለዲዛይን ሥራ | 10,000,000 .00 |
| 11 | ለኢንተሪየር ሥራዎች | 300,000,000.00 |
| የኮርፖሽኑን የሰው አቅም ለማሳደግ ለይዘት ሥራዎች ለማሻሻል እንዲቻል፡፡ | | |

| | | |
|---|---|---|
| 12 | ለስልጠና ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ግዢ | 30,000,000.00 |
| 13 | ለሰው ኃይል አቅም ግንባታ | 100,000,000.00 |
| **በተቋሙ አስፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት ለካፒታል ግዢ የሚያስፈልግ አጠቃላይ ብር መጠን ድምር** | | |

## በጀት ማጠቃሊያ

| ተ.ቁ | በጀት ርዕስ | ብር |
|---|---|---|
| 1 | መደበኛ ባጀት ድጋፍ | 500,000,000.00 |
| 2 | ካፒታል በጃት ድጋፍ | 1,320,000,000.00 |
| | **ድምር** | 1,820,000,000.00 |